# የውጋዴኑ ጀግና ደጃዝማች ዑመር ሰመትር

ከ አባተ ማንደፍሮ ኃይሉ

ወደ ኋላ ያለውን የሀገራችን ታሪክ ቢፈተሽ የምናገኘው በአብዛኛው የጦርነት ታሪክ ነው፡፡ ባሕር አቋርጠው ... ድንበር ተሻግረው የሀገራችንን መሬት በቅኝ ግዛት ለመርገጥ የሞከሩ ሀገራት በርካታ ናቸው፡፡ምንም እንኳ ከሀገራችን ታሪክ አብዛኛው በጦርነት ታሪክ ተሸፈነ ነው ቢባልም ሀገራችን ኢትዮጵያ ግን ለአንድም ጊዜ ከድንበሯ ውጭ ያደረገችው ጦርነት የለም ::የሌላ ሀገርን መሬት ለመውረር ያደረገችው አንድም ጦርነት እንደሌለ የዓለም ድርሳናት ይመሰክራሉ፡፡ ሀገራችንን በተደጋጋሚ በመውረር ከሚጠቀሱት ሀገራት መካከል አውሮፓዊቷ ጣሊያን አንዷ ናት፡፡

በ1888 ዓ.ም በዳግማዊ አጤ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት በኢትዮጵያና በኢጣሊያን መካከል ተካሂዶ ለነበረው ጦርነት ዋናው መነሻ ምክንያት የውጫሌ ውል 17ኛው አንቀፅ በአማርኛና በጣሊያንኛ የያዘው ትርጉም የተለያ መሆኑ ነው፡፡ሚያዚያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም ወሎ ውስጥ ቦሩ ሜዳ የተፈረመው ይህን በታሪክ ‹‹የውጫሌ ውል›› ተብሎ የተመዘገበውን ውል በጣሊያን በኩል የፈረመው ካውንት አንቶኒዮ ሲሆን አስተርጓሚው ደግሞ ቀኛዝማች ዮሴፍ ነበሩ፡፡ሃያ አንቀፅ የነበረውና በሁለቱ ሀገራት የተፈረመው ይህ ውል 17ኛው አንቀፅ ለአድዋ ጦርነት ምክንያት ቢሆንም ኢትዮጵያ በጦርነቱ አሸናፊ ናት፡፡

በወርሃ የካቲት 1888 ዓ.ም አድዋ ላይ በተካሄው ጦርነት ተማርከው የጠላት ወታደር ሳይጨምር 7560 የጣሊያን ሰራዊት አባላት የሞትና መቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል፡፡በንጉስ ኡምቤርቶ ዘመን ጠ/ሚ የነበሩት ክሪስፒ ወደ አድዋ ያዘመቷቸው የጦር አለቆች ማለትም ጄ/ል ቤሪያቴሪ :ጄ/ል ዳቦርማዳ፡ ጄ/ልአሪሞንዴ፡ጄ/ል ባልዲሜራ፡ጄ/ል አልበርቶኒ በአድዋ ጦርነት ላይ የሽንፈት ካባ ስላከናነቧቸው የሀፍረት ማቅ ለብሰው ሥልጣናቸውን ለመልቀቅ ተገደዋል ፡፡

ይህ ከሆነ ከ40 ዓመት በኋላ በ1928 ዓ.ም በቬኔቶ ሙሶሎኒ ትመራ የነበረውን ጣሊያን ደግሞ ወረራ ብትፈፅምም እንደ አድዋው በለስ ሳይቀናት እየመረራትም ቢሆን ደግሞ የሽንፈት ፅዋን ለመጨለጥ ተገዳለች፡፡

ሁለተኛው የኢጣሊያንና የኢትዮጵያ ጦርነት ከመጀመሩ አንድ ዓመት በፊት ህዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም የወልወል ግጭት ተደረገ፡፡ የእዚህ ግጭት መነሻ ምክንያት ነው ባለታሪኩን የደጃዝማች ዑመር ሰመተርን የወለደው፡፡የግጭቱ መነሻ ምክንያት ደግሞ የሚከተለው ነው፡፡

በኢትዮጵያና የእንግሊዝ ሶማሊላንድ መካከል ያለውን የድንበር ወሰን በደንብ ለማካለል በሁለቱ ወገኖች መካከል ስምምነት ይደረጋል፡፡ ይህን የጋራ ስምምነት በተግባር ላይ ለማዋል ከኢትዮጵያ በኩል ፊታውራሪ ተሰማ በንቲ በእንግሊዝ በኩል ክሊፎርድ ዋነኛ የወሰን ተከላካዮች ይሆናሉ፡፡ በወልወል በኩል አልፈው የአካባቢው ነዋሪዎች ከብቶች ሣር የሚግጡበት እና ውሃ የሚጠጡበትን ስፍራ ለመመርመር በእዚያ በኩል ሲልፉ ያልታሰበ ነገር ይገጥማቸዋል፡፡

በአካባቢው የነበረውን የኢጣሊያ ጦር ይመራ የነበረ ካፒቴን ቺማሩታ በ1920 ዓ.ም የተደረገውን የወሰን ስምምነት በመጣስ 100ኪ.ሜ. ያህል ወደ ውስጥ ገብቶ ‹‹ደብት›› በመባል የሚመራውን ጦር በመያዝ የኢትዮጵያና እንግሊዝ የወሰን ተከላካዮች እንዳያልፉ ከለከለ፡፡

እነ ፊታውራሪ ተሰማ ያሉበት ቦታ የኢትዮጵያ መንግስት ግዛት መሆኑን ቢያረጋግጡለትም ካፒቴን ቺማሩታ ግን ፍቃደኛ ለመሆን አልቻለም፡፡ ‹‹ ... ከመንግስቴ ታዝዤ ነውና የያዝኩት ከእዚህ እልፍ ማለት አልችልም›› ብሎ በእነ ፊታውራሪ ተሰማና በእነ ፊታውራሪ አለማየሁ ላይ ድንገተኛ አደጋ ጣለ፡፡ በእዚህ ዕለት የተደረገው ጦርነት የአውሮፕላንም ድብደባም ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ወታደሮች ይህንን የመሰለ ጦርነት የተዘጋጁበት አልነበረም፡፡ለውጊያው ባይዘጋጁበትም ኢትዮጵያውያን ወታደሮች እስከ ምሽት ድረስ በጀግንነት ሲወጉ ውለዋል፡፡ የኢጣሊያ ጦር የውጊያ አውሮፕላኖች በሚያካሂዱት የአየር ድብደባ ብዙ ሰው ከኢትዮጵያ በኩል ስለተጎዳ ወደ ኋላ መመለስ ግድ ሆነባቸው፡፡ በእዚህ የወልወል ግጭት ፊታውራሪ አለማየሁ ጎሹን ጨምሮ 170 ኢትዮጵያውያን ተገደሉ፡፡ ከጠላት ወገን ደግሞ 75 የሚሆኑት ሞተዋል፡፡

የኢጣሊያን መንግስት በ1920ዓ.ም የተደረገውን የወሰን ስምምነት ጥሶ በታሪክ የወልወል ግጭት ተብሎ ለተመዘገበው ታሪክ ግጭት ምክንያት መሆኑ ሳያንሰው የኢትዮጵያ መንግስት የ200 ሺህ ብር ካሳ እንዲከፍለው የደጃዝማች ዑመር ሰመተርን እጅ ይዞ ለጣሊያን እንዲሰጥ ፊታውራሪ ሽፈራው ከሹመታቸው እንዲሻሩ ደጃዝማች ገብረማሪያም ጋሪ ወልወል ድረስ ወርደው ቺማሩታ ይቅርታ እንዲጠይቁ የሚል ጥያቄ አቀረበ፡፡...የኢትዮጵያ መንግስት እንዲያስረክብ የተጠየቁት ደጃዝማች ዑመር ሰመትር ማን ናቸው?....ይህን ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

ደጃዝማች ዑመር ሰመትር ከአድዋ ጦርነት አስራ ሰባት ዓመት በፊት በ1871 ዓ.ም ከኢትዮጵያውያን ወላጆቻቸው ከልካዩ በተባለ ቦታ ነው የተወለዱት፡፡ደጃዝማች ዑመር ሰመትር የሀገራቸውን ጠላት ለመመከት ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገዋል፡፡

በቀብሪደሀርና በዋርዴር መካከል የምትገኘው ገድለ ጉቤ የደጃዝማች ዑመር ሰመትር የሰለጠነ ጦር የመሸገበት ነበር፡፡*(የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ በ1970ዎቹ ከ ሶማሊያ ጋር ተደርጎ በነበረው ጦርነት ገድለ ጉቤን ተዋግቶበታል፡፡ ትልቁና ትንሹ ገድለ ጉቤ የሚባሉ ሁለት ቦታዎች በእዚያን ጊዜ ከፍተኛ ውጊያ የተካሔደባቸው ስፍራዎች ነበሩ)*፡፡ ከነበረበት ገድለ ጉቤ የሚነሳው የደጃዝማች ዑመር ሰመትር ጦር ባልታሰበ ሰዓት በፍጥነት እየተንቀሳቀሰ በጠላት ጦር ላይ በተለያየ ጊዜ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል፡፡

ከወልወል ግጭት ጀምሮ የዑመር ሰመትርን እጅ የመያዝ ፍላጎት የነበረው የኢጣሊያ ጦር በተለያየ ጊዜ ለመያዝ ሙከራ አድርጎ አልተሳካለትም ነበር፡፡ ኤልቡር በተባለ ቦታ ላይ ከሆነለት ለመማረክ አለዚያም ለመግደል በስድስት የሻለቃ ጦር ደጃዝማች ዑመር ሰመትርን አስከበበ፡፡ ዑመር ሰመትር የከበባቸው የጠላት ጦር ከእሳቸው ሠራዊት ኃይል በላይ መሆኑን ሲረዱ ከከበባው ሾልከው አመለጡ፡፡በ1930 ዓ.ም የተጠናከረ ሠራዊታቸውን ይዘው ጠላት ላይ ድንገተኛ ማጥቃት የጠላት ጦር ከፍተኛ ጉዳት ደረሰበት፡፡በዑጋዴን በረሃማ አካባቢዎች ጦራቸውን ይዘው እየተዘዋወሩ የጠላት ጦር ማስጨነቅ የየዕለት ተግባራቸው ሆነ፡፡ በቆራሄ ሜዳና በሌሎችም የዑጋዴን አውራጃዎች ለሀገራቸው ነጻነት መከበር ተፋልመዋል፡፡

የሀገራቸው መደፈር ቁጭት ውስጥ ከቷቸው በምስራቁ የሀገራችን ክፍል ከጠላት ጋር ትንቅንቅ የገጠሙት ደጃዝማች ዑመር ሰመትር በአንድ ዕለት ውጊያ በስድስት ጥይት ተመቱ፡፡የተመቱባቸው ጥይቶች ከሰውነታቸው ውስጥ ያልወጡ በመሆኑ እንደልባቸው ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ መዋጋት አልቻሉም፡፡... እያደር ህመማቸው እየበረታ ሄደ፡፡በጊዜው ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው ሁኔታ ህክምና የሚያገኙበት ቦታ አልነበረም፡፡...ያለው ዕድል ውጭ ሀገር ሄዶ መታከም ነበር፡፡...የተዋጉላትን ሀገር የደሙላትን መሬት በህክምና ምክንያት ጥለው ለመሄድ ተገደዱ፡፡መጀመሪያ ወደ ሀርጌሳ ተጓዙ ከእዚያም ወደ ኬንያ ቀጥሎም ወደ እንግሊዝ አቀኑ፡፡

ከአምስት ዓመታት ያላሰለሰ ጦርነት በኋላ ዳግም ኢትዮጵያን የወረረው የጠላት ጦር የሽንፈት ጽዋ ለመጨለጥ ተገደደ፡፡ በመላው ኢትዮጵያ የሰላምና የነፃነት አየር ነፈሰ፡፡በእዚህ ወቅት ነበር ዑመር ሰመትር ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ የተመለሱት፡፡

ዑመር ሰመትር ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ ተሰጥቷቸው የዑጋዴንና የጅጅጋ ገዥ ሆነው ተሾሙ፡፡የተዋጉላትን...የደከሙላትን ሀገር በሰላሙ ጊዜ በቅንነት ማገልገል ጀመሩ፡፡ በእዚያ በአርበኝነት ጦርነት ዘመን ለሀገራቸው ሲፋለሙ በስድስት ጥይት የተመቱት ዑመር ሰመትር ሁሉም ጥይቶች ከሰውነታቸው ውስጥ አልወጡም ነበር ፡፡ ይህ ደግሞ በጤናቸው ላይ ችግር አስከተለ፡፡በተለያየ የህክምና ተቋማት ቢታከሙም እንደተመኙት ግን መዳን አልቻሉም፡፡

ምንግዜም በታሪክ ውስጥ ደምቆ የሚታይ አኩሪ የጀግንነት ተግባር የፈጸሙት የዑጋዴኑ ጀግና ደጃዝማች ዑመር ሰመትር መጋቢት 6 ቀን 1936ዓ.ም በተወለዱ በ65ኛ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ ሀረር ከተማ በሚገኘው የአብዱል መኪ መካነ መቃብር በሙሉ ወታደራዊ ሥነ ሥርዓት ቀብራቸው ተፈጽሟል፡፡

ደጃዝማች ዑመር ሰመትር ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸው በፊት የተናገሩትን አዲስ ዘመን ጋዜጣ በመጋቢት 5 ቀን 1977ዓ.ም በሚከተለው ሁኔታ አስፍሮት ነበር፡፡

**‹‹ ...የሀገሬውን ሕዝብ የፈጀው ጠላት በጀግኖች ክንድ ተረግጦ ሲወጣ ተመልክቻለሁ፡፡ የመገዛት የመዋረድና የመረገጥ ዕድል ምን ዕንደሆነ አይቻለሁ፡፡ እንደ ጠራራ ንብ በየምሽቱ እየገቡ የሚነድፉ ኢትዮጵያውያን ዘር በመሆኔ ኮርቻለሁ፡፡ በታሪክ የሰማሁትን የአድዋ ጀግኖች ጀብዱ ለማስመስከር ልጆቻቸው በዑጋዴን የጣሊያንን አንገት ሲቆርጡ አይቻለሁ፡፡ የዚህ ሕዝብ ልጅ በመሆኔ እኮራለሁ፡፡የማዝነው ግን መላው ሶማሊዎች ተባብረው የአንዲት ኢትዮጵያ ልጅ ሆነው በአንድ ሰንደቅ አላማ ስር ሲጠቃለሉ ሳላይ በመሞቴ ነው በመቃብርም ውስጥ ምኞቴ ይህ ነው፡፡...››**

*ይህን ፅሁፍ ለማዘጋጀት 1 -የተክለፃድቅ መኩሪያ ‹የኢትዮጵያ ታሪክ› እንዲሁም*
*2 -የመስፍን ኃይሌ ‹አደራ› መፅሀፍትን መጠቀሜን በአክብሮት መግለጽ እወዳለሁ*

*አባተ ማንደፍሮ ኃይሉ ‹ዋስትና› የተባለው የአረጋውያን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነው፡፡*

*መስከረም፣2004 / Sep 2011/*